አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

፳ኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ሀምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No 55
ADDIS ABABA 12th JULY, 2017

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፶፭/፪ሺ፱**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺህ፪ (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ----ገፅ**

**CONTENTS**

**Proclamation No 55/2017**

**A Proclamation to further Amend the Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment Proclamation page……**

## አዋጅ ቁጥር ፶፭/፳ሺ፱

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ (1) (ሀ) መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## PROCLAMATION No 55/2017

## A PROCLAMATION TO FURTHER AMEND THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT MASS MEDIA AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to further amend the Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment Proclamation No.20/2009, as amended;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 14 sub-article (1) (a) of Revised Charter Proclamation No. 361/2003 (as amended), the Addis Ababa City Government Council hereby proclaimed as follows

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭

Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ……………….

Unit price ………………...

**፩ <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፶፭/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

**፪ <u>ማሻሻያ</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፳/፪ሺ፪ (እንደተሻሻለ) እንደገና እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩ የአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተተክቷል፤

፩. "ኤጀንሲው በየጊዜው ከተቋሙ ዕድገት ጋር እየታየ የብሮድካስት ሚዲያውን፤ የፕሬስ ሚዲያውን፤ የኢንጂነሪንግ ዘርፉን፤ የድረ-ገፅ እና አዲሱን ሚዲያ በተናጥልና በመቀናጀት የሚመሩ፤ የሚደግፉና የሚያስተባብሩ ምክትል ስራ አስኪያጆች ይኖሩታል፡፡"

፪ የአዋጁ አንቀፅ ፲፫ ንዑሥ አንቀፅ (፬) ተሰርዟል፡፡

፫ የአዋጁ አንቀፅ ፲፬ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፲፬ ተተክቷል፤

"፲፬. <u>**ስለ ዳይሬክተሮች**</u>

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the 'Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment (Amendment) Proclamation No 55/2017'

2. **Amendment**

The Addis Ababa City Government Mass Media Agency Establishment Proclamation No. 20/2009, as amended, is hereby further amended as follows:

1. Sub-article (1) of Article 13 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (1);

   1. "The Agency shall have, in view of its development from time to time, Deputy Managers who, individually and incoordination, direct, assist and coordinate broadcast media, press media, engineering sector, web-site and addis media."

2. Article (13) sub-article (4) of the Proclamation is deleted.
3. Article 14 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 14:

"14. Directors

ኤጀንሲው፡-

ሀ. የብሮድካስት ሚዲያን የሚመሩ፤

ለ. የፕሬስ ዘርፉን የሚመሩ፤

ሐ. የኢንጂነሪንግ ዘርፉን የሚመሩ፤

መ. የድረ ገፅና አዲሱ የሚዲያ ዘርፉን የሚመሩ፤

ሠ. የማስታወቂያና ገበያ ልማት ዘርፉን የሚመሩ፤

ረ. አስተዳደር፣ የፋይናንስ እና ሌሎች ዘርፎችን ለመምራት አስፈላጊ የሆኑ፤ ዳይሬክተሮች ይኖሩታል፡፡

፬ የአዋጁ ከአንቀፅ ፲፭ እስከ አንቀፅ ፲፱ ድረስ ያሉት በሙሉ ተሰርዘዋል፤
የአዋጁ አንቀፅ ፳፣ ፳፩፣ ፳፪፣ ፳፫ እና ፳፬ እንደአግባቡ አንቀፅ ፲፭፣ ፲፮፣ ፲፯፣ ፲፰ እና ፲፱ ሆነዋል፡፡

**፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከሀምሌ ፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሀምሌ 5 ቀን 2009 ዓ.ም**

**ድሪባ ኩማ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

The Agency shall have Directors who are necessary to direct:

a) the broadcast sector;
b) the press sector;
c) the engineering sector;
d) the website and Addis media sector;
e) the advertisement and market development sector;
f) The administration, finance and other sectors.”

4. Articles 15-19 of the Proclamation are deleted.
Articles 20, 21, 22, 23 and 24 of the Proclamation are renumbered as Articles 15,16,17,18 and 19 respectively.

3. **Effective Data**

This proclamation shall enter into force as of the 12th day of July, 2017.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of July, 2017**

**DiribaKuma**

**Mayor of the Addis Ababa City**